# በ1969 ዓ. ም. የወጣው የገንዘብና የባንክ አዋጅ ለውጦች ውጤቶች

በበፈቃዱ ደግፌ*

## መ ግ ቢ ያ

የገንዘብ ታሪክ በኢትዮጵያ ውስጥ ከአክሱም ዘመነ መንግሥት ጀምሮ የረጅም ጊዜ ዕድሜ ያለው ቢሆንም በአንፃሩ[1] አጠቃላይ ገንዘብ ነክ ሕጎችና ተቋሞች መታወቅ የጀመሩት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው ። በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ባንክ የአበሻ ባንክ በመባል የሚታወቀው የግብጽ ብሔራዊ ባንክ ቅርንጫፍ ነበር ። ይህ ባንክ እ.ኤ.አ. ከየካቲት 16/1905 ዓ.ም. ጀምሮ ለአገሪቱ የንግድ እንቅስቃሴ በሩን ክፍት በማድረግ በአምስት መቶ ሺህ (500,000) ፓውንድ ካፒታል ሥራውን ጀመረ ። በጥቅምት ወር 1931 ዓ.ም. እ.ኤ.አ በኢትዮጵያ መንግሥት ተገዝቶ የኢትዮጵያ ባንክ (ባንክ ኦፍ ኢትዮጵያ) በሚል አዲስ ስያሜ ተግባሩን ሲቀጥል በዚህም ባንኩ ፤ አገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ብቸኛ ባለ ንብረትነቱን የያዘችበት ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ አህጉር የመጀመሪያው ከባዕድ እጅ ነፃ የሆነ ብሔራዊ ማዕከላዊ ባንክ ሊሆን ቻለ ።

የኢትዮጵያ ባንክ እ.ኤ.አ. በ1936 ዓ.ም. ሲፈርስ እስከ 1942 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) በቦታው የተተካ ምንም ዓይነት ኢትዮጵያዊ ባንክ ያልነበረ ቢሆንም በዚህ ጊዜ የባንክ አገልግሎቶች አልተቋረጡም ። ባንኮ ዲ. ኢታሊያ ፤ ባንኮ ናሲዮናል ዴል ላቦሮ ፤ ባንኮ ዲ. ሮማና ባንኮ ዲ. ናፖሊ የተባሉት አራት የኢጣሊያ ባንኮች ቅርንጫፎች አገልግሎት ሲሰጡ ነበር ። ከነዚህም ሁለቱ አገልግሎታቸውን ሲያቋርጡ ባንኮ ዲ. ሮማና ባንኮ ዲ. ናፖሊ እ.ኢ.አ. በጥር ወር 1975 ዓ. ም. እስከ ተወረሱበት ጊዜ ድረስ ተግባራቸውን ቀጠሉ ። በ1941 ዓ.ም. (እ.አ.አ.) ጣሊያኖች ወጥተው እንግሊዞች ወደ አገራችን ሲገቡ የእንግሊዙ ባርክሌይስ ባንክ (ባርክሌይስ ባንክ ኦፍ ብሪተን) የተሰኘው ባንክ የእንግሊዝ ወታደሮችን ዱካ ተከትሎ በመግባት ቅርንጫፍ ከፍቶ እስከ 1942 ዓ.ም. ድረስ ሲሠራ ቆየ ። በድህረ ሁለተኛ ዓለም ጦርነት ፤ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ባንክ በ1942 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) በአዋጅ የተቋቋመው (አዋጅ ቁ. 21/42) የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ (ስቴት ባንክ ኦፍ ኢትዮጵያ) ነበር ። ይህም ባንክ እስከ 1963 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) ድረስ የንግድና የማዕከላዊ ባንኮችን ተግባራት በማዋሃድ ሲሠራ ቆየ ።

በ1963 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) የወጣው የገንዘብና የባንክ አዋጅ ከዚህ በታች ገባአ 1 ብለን የምንጠራው አዋጅ ቁ. 206/63 የንግድና የማዕከላዊ አገልግሎቶችን በመለየት ፤ የኋለኛው ማለትም የማዕከላዊ ባንኩን ዘርፍ በዚሁ ዓመት በትዕዛዝ በተመሠረተው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ኃላፊነት ሥር አዋለው ። ምንም እንኳ ከ1963 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) በፊት ገንዘብና ገንዘብ ነክ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ሕጎች ቢኖሩም የአገሪቱ የገንዘብ ፖሊሲ በግልጽ የተብራራውና አመራሩም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሥር ሆኖ የተደላደለ ሥርዓት ሊይዝ የቻለው እላይ በተጠቀሰው በገባአ 1 መሠረት ነው ።

የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት በታኅሣሥ ወር 1975 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) የሚከተለው የኅብረተሰባዊነት ፍልስፍና መሆኑን በማወጅ ለዚህም ግብ መምታት የሚያስችል የኤኮኖሚ ፖሊሲ ቀየሰ ። ከብዙ በጥቂቱ የዚህ ኤኮኖሚ ፖሊሲ ዓላማ ለኢኮኖሚ ግንባታ እጅግ አስፈላጊ የሆኑትን ከፍተኛ የማምረቻ መሣሪያዎች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የሚውሉበት ዘዴ የታቀደበት ነበር ። ከላይ የተጠቀሰውን ተግባራዊ ለማድረግ ጊ.ወ.መ. በጥር 1 ፤ 1975 (እ.አ.አ.) ዓ.ም. ሶስት የንግድ ባንኮችን ፤ አሥራ አንድ የሚሆኑ የመድን ድርጅቶችንና ሁለት ሁለገብ የገንዘብ ድርጅቶችን በመንግሥት ቁጥጥር ሥር በማድረግ የኅብረተሰቡን ፍላጐት ሙሉ በሙሉ ለማርካት በሚቻልበት መንገድ እንዲያዙ ወሰነ ። የተወረሱት የመድን ድርጅቶች ቀድሞውኑ የመንግሥት ከሆኑት የመድን ድርጅቶች ጋር በመዋሃድ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በሚል መጠሪያ ታወቁ ። ሁለቱ ሁለገብ የገንዘብ ድርጅቶችም ተዋህደው የቤትና የቁጠባ ባንክ ተቋቋመ ። የመንግሥት የሆኑ የእርሻና ኢንዱስትሪ ባንኮችም እንደገና ተቋቁመው ለእርሻውና ለኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ ዕድገት አስፈላጊውን ብድር የመስጠቱን ሥራ ተያያዙት ። ንግድ ባንኮችን እንደገና የማቋቋሙ ተግባር በሁለት የዕድገት ደረጃዎች ውስጥ አልፎአል ። የመጀመሪያው የተወረሱት ሶስት ባንኮች መዋሀድና አዲስ ባንክ መባል ሲሆን የመጨረሻው ደረጃ ደግሞ ንብረትነቱ የመንግሥት የሆነ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሚል መተካቱ ነው ። የገንዘቡ ክፍለ ኤኮኖሚ ያሳየው የመጨረሻ ዕድገት በ1963ቱ (እ.አ.አ.) የገንዘብና የባንክ አዋጅ (ገባአ1) በ1976 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. የገንዘብና የባንክ አዋጅ ከዚህ በታች ገባአ2 ብለን በምንጠራው መተካት ነው ።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በገባአ 1 ፤ 1963ቱ ቻርተርና በዚሁ ዓመት አዋጅ ቁ. 211/63 እና በገባአ 2 መካከል ያሉትን ልዩነቶች ጨምቆ ለማሳየት ሙከራ ሲደረግ በአዋጆቹ የተፈጠሩ አዳዲስ ሁኔታዎች በኢኮኖሚው የተንጸባረቁትን ገፅታዎች አብሮ ለማየት ጥረት ተደርጓል ። በክፍል አንድ ውስጥ የ1963ቱንና የ1976ቱን አዋጆች በማነጻጸር አጠቃላይ ግምገማ ሲደረግ ትኩረት የተደረገው በልዩነቶች ላይ ነው ። በዚህም ውስጥ ለአቀራረብ እንዲያመች የ1976ቱን አዋጅ መዋቅር ተከትለናል ። ክፍል ሁለት ደግሞ በአዋጆቹ ሳቢያ የተከሰቱት ዋነኞቹ ለውጦች ያስከተሉአቸውን ሁኔታዎች ያጠናል ።

## 1. በ1976 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. በወጣው የገንዘብ አዋጅ የተደረጉ ዋና ዋና ለውጦች

(እ.ኤ.አ.) ከ1963 ዓ.ም. ወደዚህ ያለው የገንዘብ ፖሊሲና አመራሩ በሁለት አዋጆች[2] ሥር በተጠቃለሉ 78 አንቀጾችና በአንድ ትዕዛዝ[3] ሥር ተዘርዝሯል ።

እነዚህም አዋጆች ገንዘብና ባንክን እንዲሁም የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሬን የሚመለከቱ ሲሆኑ ትእዛዙ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተቋቋመበት ቻርተር ነው[4]። ሁለቱም አዋጆች ማለትም የ1963ቱና የ1976ቱ አንቀጾች ብሔራዊ ባንኩን ያቋቁማሉ ፤ የሕግ ሰውነትም ያጐናጽፉታል ፤ እንዲሁም ሥልጣኑንና ተግባሩን ያብራራሉ ። በሁለቱም አዋጆች መሠረት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የአገሪቱን የገንዘብና የባንክ ሥርዓት ይቆጣጠራል ። ሆኖም ግን የባንኩን ተግባርና ሥልጣን በሚመለከት ረገድ ገባአ 2 ከገባአ 1 የበለጠ ግልጽ ነው ። የ1963ቱ ድንጋጌዎች ባንኩን የገንዘብ ኖቶችና ሳንቲሞች ብቸኛ አመንጪ ሲያደርጉት[5] በተጨማሪም ደግሞ ለሚከተሉት ተግባራት ሥልጣን ያሰጡታል[6]። እነዚህም በአገልግሎት ላይ የሚውለን የገንዘብ መጠን የመቆጣጠር ፤ የወለድ መጠንን የመወሰን ፤ የአገሪቱን ዓለም አቀፋዊ የመጠባበቂያ ሂሳብ የመምራት ፤ የገንዘብን ዋጋ መረጋጋት በሚያግዝ ዓላማ ለባንኮች የሥራ ፈቃድ የመስጠትና ተግባራ

ቸውን የመቆጣጠር[6]፣ ለተመዛዘነ የምጣኔ ሀብት ዕድገት ምቹ ሁኔታን ሊፈጥር በሚችል አኳኋን የክሬዲትና የገንዘብ ምንዛሪ ሁኔታዎች የመቆጣጠር ናቸው[7]። በዚሁ ረገድ ገባአ 2 ከዚህ ይልቅ ጠለቅ ባለ ሁኔታ ባንኩ ከላይ የተዘረዘሩትንና ሌሎችንም የተሰጡትን ሥልጣኖች በተግባር ለመተርጐም የሚከተላቸውን ዓላማዎች ይገልጻል ። ይህም በብሔራዊ ደረጃ ከተነደፈው ፕላን ጋር በሚጣጣም ዓይነት ከፍተኛ ዕድገት ፤ የሥራ ዕድልና የተረጋጋ የዋጋ ሁኔታን ለመፍጠር ይሆናል[8]። የብሔራዊ ባንኩ ሥልጣን በአዋጁ አንቀጽ ዘጠኝ ሥር በተዘረዘሩ አሥራ ስድስት ንዑስ አንቀጾች የተገለጸ ሲሆን በነዚህም አንቀጾች ባንኩ የኀብረት ይዞታ ባላቸው የሥራ ክፍሎች[9] ውስጥ ለባንኩ ክፍት የሆነ ሂሳቦችን የመቆጣጠር[10]፣ በቁጥጥራቸው ሥር ያለን ሀብት አግባብ ባልሆነ መንገድ ለሚያውሉ ድርጅቶች ባንኮችና የገንዘብ ድርጅቶች ብድር የመከልከል[11] መብት የተሰጠው ሲሆን ዓላማውም የአገሪቱን ሀብት ጠቃሚ ለሆነ ጉዳይ በተቀላጠፈ ሁኔታ ተግባር ላይ ለማዋል ታቅዶ ነው[12]። በዚህም ረገድ ገባአ 2 የባንኩን ተግባራት ይበልጥ በማያሻማ መንገድ ሲያብራራው ሥልጣኑን ግልጽ በሆነ መንገድ ያስቀምጠዋል ።

የአዋጁ ምዕራፍ ሶስት በ1963ቱ ቻርተር[13] ውስጥ የተጠቀሱትን የካፒታል ፤ የመጠባበቂያና የሂሳብ ማስታወቂያዎችን ይመለከታል[14]። በመሠረቱ የሚለየው ግን በካፒታሉ መጠን መጨመርና በትርፍ ስርጭት አያያዝ[15] ላይ ነው ።

የምዕራፍ አራት ይዘት የባንኩን ድርጅታዊ መዋቅርና አስተዳደር የሚመለከት ሲሆን ይህም ጉዳይ በቻርተሩ ውስጥ በቅድሚያ ተጠቅሷል[16] ። በሁለቱም አወቃቀር መሠረት ባንኩ የሚተዳደረው በዲሬክተሮች ቦርድ ሲሆን የተቀሩት አንቀጾች አስተዳደርና ባጠቃላይ በድርጅታዊ መዋቅሩ ላይ ያተኩራሉ ።

ምዕራፍ አምስት በባንኩና በመንግሥት መካከል የሚኖረውን ግንኙነት ያብራራል ። ይህም በገባአ 1 ውስጥ በምዕራፍ ሶስት የተገለጸ ሲሆን ከፊሉ በ1969 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) ማሻሻያ የተደረገላቸው ናቸው[17]። በዚህም መሠረት ባንኩ ገንዘብ ነክ ጉዳዮችን በሚመለከት የመንግሥት ወኪልና ባንክ ሆኖ ያገለግላል ። በእንጻሩም በመንግሥት ስም ገንዘብ ያበድራል ፤ ገንዘብ ይቀበላል እንዲሁም አስፈላጊ ክፍያዎችን ያከናውናል ።

የብድርን አሰጣጥ በሚመለከት በገባአ 1 (እንደተሻሻለው) ባንኩ ለመንግሥት የሚሰጠው ብድር በሚከተሉት መንገዶች ይሆናል ።

ሀ/ ቀጥታ በማበደር ለ/ የግምጃ ቤት ሰነዶችን በመግዛትና ሐ/ የመንግሥት ዕዳ ሰነዶችን (ቦንዶችን) በመግዛት ነው[18]።

ሁለተኛ የብድሩ መጠን ገባአ 1 (እንደተሻሻለው) ለመንግሥት የሚሰጠውን ቀጥታ ብድር ካለፈው የበጀት ዓመት መደበኛ የመንግሥት ገቢ ከመቶ ሃያው እጅ (20%) ሊበልጥ እንደማይችል ይወስናል ። ይህም በዓመት ከመቶ ሶስት (3%) ሊያንስ የማይችል ወለድ የሚታሰብበት ሆኖ የወለዱም መጠን በባንኩና በገንዘብ ሚኒስቴር መካከል በሚደረግ ስምምነት ይወሰናል ። በዚህ አዋጅ መሠረት ማለትም ገባአ 1 (እንደተሻሻለው) መንግሥት ተጨማሪ ብድር ለማግኘት የሚችለው ያለበትን ዕዳ በቅድሚያ አጠናቅቆ ሲከፍል ብቻ ነው[19]።

ገባአ 2 ግን የብድሩን መጠን ከመደበኛ የመንግሥት ገቢ አንጻር ያለውን ሚዛን ከሃያ በመቶ (20%) ወደ ሃያ አምስት በመቶ ከፍ ሲያደርገው በመቶ ሶስት የተባለውንም ወለድ ጣሪያው አድርጐታል ። እንደዚሁም የቀድሞውን ዕዳ ማጠናቀቅን ለተጨማሪ ብድር መስጠት እንደ ቅድመ ሁኔታ አይቆጥረውም[20]።

እንዲሁም በገባአ 1 ((እንደተሻሻለው) መንግሥት በግምጃ ቤት ሰነዶች ሽያጭ ከባንኩ ወይም በባንኩ በኩል ብድር ሊያገኝ ይችላል[21]። የሰነዱም ዋጋ መጠን ካለፈው የበጀት ዓመት መንግሥት ከሰበሰበው መደበኛ ገቢ ከአሥራ ሁለት ተኩል በመቶ (12½%) እንደማይበልጥ ሲወስን ገባአ 2 ግን ይህንን ሚዛን ወደ ሃያ በመቶ (20%)ከፍ አድርጎታል[22]።

መንግሥት ብድር ሊያገኝበት የሚችለው ሶስተኛው መንገድ ደግሞ የዕዳ ሰነዶች ሽያጭ ነው ። መጠኑም የባንኩን ካፒታል ሶስት እጅ የጠቅላላ መጠባበቂያ ሂሳብና ሰማኒያ ሁለት ሚሊዮን ብር[23] ያህል ነበር ። በገባአ 2 ግን ብድሩ የሚተመነው ባለፈው የበጀት ዓመት መንግሥት የሰበሰበው መደበኛ ገቢ መሠረት ሆኖ ሚዛኑም በመቶ ሃምሳ (50%) እንዲሆን ተደርጓል[24]።

ምዕራፍ ስድስት ባንኩ ከሌሎች ባንኮችና የገንዘብ ድርጅቶች ጋር ያለውን ግንኙነት የሚመለከት ሲሆን እርሱም ሶስት ክፍሎች አሉት ።

ሀ/ የክሬዲት ሥራን ማስተባበርና መቆጣጠር

ለ/ የክሬዲት ትራንዛክሽን ፤ በአደራ የሚቀመጡ ንብረቶችና ከዚህ ጋር ዝምድና ያላቸውን ተግባሮች ማከናወን የሚመለከቱና

ሐ/ ከኢንተርናሲዮናል የመጠባበቂያ ንብረቶች ጋር የተያያዙ ንብረቶች ሲሆን ይህ በመጨረሻ የተጠቀሰው ከቀደመው አዋጅ[25] የሚለይበት ምንም ስለሌለው ብዙም ትኩረት አይሰጠውም ። ይህም የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሬን ሥራ ለማካሄድና ይህንንም ተግባር በወኪል አማካይነት በማስፈጸም ረገድ ባንኩን ብቸኛ ባለሥልጣን ከሚያደርጉት አንቀጾች አንጻር ማለት ነው ።

ሀ/ <u>የክሬዲት ሥራን ማስተባበርና መቆጣጠር</u>

በዚህ ረገድ ሁለቱም ሕጎች[26] ተመሳሳይነት ሲኖራቸው ባንኩ የራሱንም ሆነ የሌሎች ገንዘብ ድርጅቶችን ክሬዲት የመምራት ፤ ሌሎች ባንኮችና የገንዘብ ድርጅቶች ከባንኩ የሚበደሩበትን የወለድ ተመን የመወሰን ፤ እንደዚሁም ራሳቸው በሚይዙት የማጠራቀሚያ ሂሳቦች ላይ የሚታሰበውን ወለድ የመተመን የሂሳቦቹንም መጠን ተግባርና ወቅት የመቆጣጠር ሥልጣኖች አሉት ።

እዚህ ላይ ሁለቱ ሕጎች የሚለዩባቸው ሁለት ጉልህ ነጥቦች ጥሬ ገንዘብና የመጠባበቂያ ሂሳቦችን የማኖርን አስፈላጊነት የሚመለከቱ ናቸው ። በሁለቱም ሕጎች መሠረት[27] ባንኮችና የገንዘብ ድርጅቶች ለተቀማጭነት ከተቀበሉት ገንዘብ ውስጥ የተወሰነ መጠን በጥሬ ገንዘብ ወይም በግምጃ ቤት ሰነዶችና በመሳሰሉት ገንዘብ መሰል ንብረቶች[28] መልክ በባንኩ የማስቀመጥ ግዴታ አለባቸው ። ትልቁ ልዩነት ግን በገባአ 1 የሚጠራቀመው ሂሳብ መጠን ከጠቅላላው ከመቶ ሃያ (20%) መብለጥ የማይገባው መሆኑን ሲገልጽ ገባአ 2 ግን መጠኑን ለባንኩ ይተወዋል ። በተጨማሪም ባንኮችና የገንዘብ ድርጅቶች በአጭር ጊዜ ከሚከፈለው ዕዳቸው የተወሰነ መጠን በገንዘብ መሰል ንብረቶች መልክ በባንኩ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል ። የማጠራቀሚያው ሂሳብ ጣሪያ ከጠቅላላው እዳ በመቶ ሰላሳ (30%) እንዲሆን ገባአ 1 ሲወስን በገባአ 2 ግን ውሳኔው የባንኩ ፋንታ ነው[29]

ለ/ <u>ስለክሬዲት ሥራና በአደራ ስለሚቀመጡ ንብረቶች</u>

በዚህ በኩል ሁለቱም አዋጆች ማለትም ገባአ 1 ና ገባአ 2 ባንኮችና ሌሎችም የገንዘብ ድርጅቶች ከብሔራዊ ባንክ ገንዘብ ሊበደሩ የሚችሉበትን ሁኔታዎች

ይተነትናሉ[30]። በዚሁ ውስጥ እንደተጠቀሰው ብሔራዊ ባንኩ የሐዋላ ሰነዶችን የግምጃ ቤት ሰነድ ደብተሮችንና የመሳሰሉትን ቅናሽ ወይም የቅናሽ ቅናሽ በማ ድረግ ሊሸጥ ወይም ሊለውጥ ይችላል ።

ምዕራፍ ሶስት ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶችን ስለመቆጣጠር የሚ መለከት ነው ። በገባእ 2 ውስጥ በጣም ግልጽ በሆነ ሁኔታ ብሔራዊ ባንኩ ሌሎች ባንኮችን የማቋቋም የማዋሃድና የመቆጣጠር ሙሉ ሥልጣን የተሰጠው ስለሆነ[31] በገባእ 1 ምዕራፍ አምስት የተጠቀሰው የቁጥጥርና የፈቃድ መስጠት ተግባር በዚህኛው አዋጅ ውስጥ አልተጨመረም ። ከዚህም ሌላ በዚህ ምዕራፍ ሥር የተ ደነገጉት የቁጥጥርና ምርመራ የማድረጉ ተግባር በገባእ 1 ባንኮችን ብቻ ሲመለ ከት በገባእ 2 ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶችንም ያጠቃልላል ። እዚህ ላይ ሊጠ ቀስ የሚገባው ነጥብ አለ ። ይኸውም በገባእ 1 መሠረት በባንኮች የገንዘብ አመ ራር ውስጥ ተገቢ ያልሆኑ ነገሮች ሲከሰቱ እንደሁኔታው ቅለትና ክብደት ባንኩ፤

ሀ/ የተመረመረው ባንክ ሥራውን የሚያቃናበት እርምጃ እንዲወስድ ማስደረግ

ለ/ የተመረመረው ባንክ ተጨማሪ ተቀማጭ ሂሳቦች እንዳይቀበል ወይም ብድር እንዳይሰጥ መከልከል

ሐ/ የተመረመረው ባንክ ሥራውን ለጊዜው በከፊል ወይም በሙሉ እንዲያቆም ማድረግ እና

መ ከነጭራሹ ማፍረስ[32] ሲችል ፤ በገባእ 2 ግን አስፈላጊ መስሎ የታየውን እርምጃ ይወስዳል[33]።

በምዕራፍ ስምንት ውስጥ የተገለጹት ስለገንዘብ መደብ ልክ ስለ ሕጋዊ ገንዘብና ስለውጭ አገር ገንዘብ አስተዳደር ሲሆን ገባእ 1 ይህንኑ በአንደኛው ምዕራፍ ይዟል ። ገባእ 2 የኢትዮጵያን የገንዘብ መደብ ልክ ከዶላር[34] ወደ ብር[35] ሲለውጠው ክብደቱና ጥራቱ ሳይለወጥ ዋጋው በተጣራ የወርቅ ዱስግል 0.355468 ግራም ሆኖ እንዲጸና አድርጓል ። በገባእ 1 መሠረት የኢትዮጵያን ዶላር የወርቅ ዋጋ ይዘት ለመጨመርም ሆነ ለመቀነስ የሚቻለው በሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅራቢነቱ በንጉሠ ነገሥቱ ሲጸድቅ ነበር[36]። በገባእ 2 ግን ባንኩ ለመንግሥት ሲያቀርብ ተፈጻሚነት ያገኛል[37]።

ስለብሔራዊ ባንኩ የንብረት ሥርጭት ጉዳይ የተደረገ አንድ ጉልህ ማሻ ሻያ አለ ። ሁለቱም ሕጎች ባንኩ ከጠቅላላው ንብረቱ ከፊሉን በወርቅ ፣ በውጭ አገር ገንዘብና በግዴታ ሰነዶች ወዘተ በኢንተርናሲዮናል የመጠባበቂያ ሂሳብ እንዲያኖር ይደነግጋሉ[38]። በገባእ 1 ውስጥ በግልጽ የተመለከተው ባንኩ ከላይ በተጠቀሰው ሂሳብ ሊያኖር የሚገባው ከሚያወጣቸው የገንዘብ ኖቶች (ሳንቲሞ ችን ሳይጨምር) በተጠየቀ ጊዜ ወዲያውኑ ሊከፈል የሚችል ቢያንስ ሀያ አምስት በመቶ መሆን ይገባዋል[39]።

በገባእ 2 መሠረት ግን ባንኩ በኢንተርናሲዮናል የመጠባበቂያ ሂሳብ የሚኖረው ንብረት ፣

ሀ/ ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡት አስፈላጊ ዕቃዎች

ለ/ የውጭ አገር ግዴታዎችንና ዕዳዎችን ለመክፈል የሚያስችል

ሐ/ ወደ አገሪቱ የሚገቡትን የአስፈላጊ አገልግሎቶችን የሚመጣጠን እንዲሆን ያስፈልጋል[40]።

ምዕራፍ ዘጠኝ ስለ ውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ ደምብ ሲሆን በዚሁ አዋጅና የተሻረው አዋጅ በተመሳሳይ ምዕራፍ ሥር የያዘውን የውጭ አገር ገንዘብ ምን ዛሪ የሚፈጸምበትን ሁኔታዎች ያብራራል ። በተለይም ከባንኩ ወይም ሌላ ለመ ንዛሪነቱ በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው ሰው ወይም ድርጅት በስተቀር ማንም የውጭ አገር ገንዘብ ለመያዝም ሆነ የምንዛሬ ሥራ ለማካሄድ የማይችል መሆኑን እና በእጃቸው የሚገኘውን የውጭ አገር ገንዘብ ለባንኩ የማስረከብ ግዴታ እንዳለ ባቸው ይገልጻል[41]።

የገባአ 2 ምዕራፍ አሥር ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን ፤ ስለተሻሩና በሥራ ላይ ስላሉ ድንጋጌዎች ፣ዚህና በሌሎች ሕጐች መካከል የትርጉም ግጭት ሲኖር የፊተኛው የሚጸና ስለመሆኑና ባንኩ ልዩ ልዩ ደምቦችን ማውጣት ስለ መቻሉ ፣ አዋጁን የሚተላለፍ በወንጀል የሚቀጣ ስለመሆኑ ፣ አዋጁ ስለሚጸ ናበት ጊዜ ወዘተ በዚህ ክፍል ተዘርዝሯል።[42] በተጨማሪም ባንኩ አሠራሩን በምስጢር ለመያዝ የሚያስችለው አንቀጽም ገብቷል[43]። ምሥጢራዊነት በባንክ እንዱስትሪ አሠራር የተለመደ ነገር ቢሆንም ቅሉ በኢትዮጵያ ውስጥ ግን ሕግ ካልፈቀደው በቀር የባንክ ምስጢራዊ አሠራር ከ1963 ዓ.ም. (ኢ.ኤ.አ) በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ን.ንደ ግዴታ ተገልጿል[44]።

## 2. በገባአ2 የታዩ ዋና ዋና ለውጦችና ውጤቶች

የገንዘብና የባንክ አዋጅ (ገባአ2) የአብዮቱ ሂደት ያፈለቀው አዲስ የፍልስፍናና የኢኮኖሚ ግምባታ ውጤት ሲሆን የታቀደበትም ምክንያት የአገሪቱ የገንዘብና የባንክ ሥራ ፖሊሲ ከአዲሱ ሥርዓት ጋር እንዲጣጣም ለማ ድረግና ለዚህም ዓላማ ግብ መምታት አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ለማሟላት ነው ። በገባአ2 እና በርሱ በተሻሩ ሕጐች መካከል ያለው ልዩነት በመሠረቱ ሕጐች በወጣባቸው ሥርዓቶች ሁኔታዎች ፣ እንዲሁም በታቀዱላቸው ዓላማዎች መካከል ያሉ ልዩነቶች ነጸብራቅ ሁነው መታየት ይገባቸዋል[45]።

ገባአ2 መሠረት አድርጐት የተነሳው ነፃ ኢኮኖሚን የመገንባት ብሔራዊ ዓላማ ሲሆን የዚህም ጽንሰ ሀሳብ ራስን የመቻል መርሆ ነው ። በዕድገት ጐዳና ላይ ለመንደርደሪያነት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ለማግኘት አገሪቷ የምትተማ መነው ከውጪ በሚመጡ ሳይሆን በራስ ሀብት ላይ ይሆናል ። ይህ ዓላማ በአዋጁ ውስጥ ፣ ሀ/ የገንዘብ ኖቶች ማውጣት ለ/ የገንዘብ አወጣጥንና የክሬዲት ሥራ መቆጣጠርንና ፣ ሐ/ የኢ.ት.ብ.ባ. ለመንግሥት የሚሰጠውን ብድር በሚመለከቱ አንቀጾች ተንጸባርቋል ።

### ሀ/ የኢ.ት.ብ.ባ. የገንዘብ ኖቶችን ማውጣት ስለመቻሉ

በአገሪቱ የገንዘብ ፖሊሲ ዕድገት ውስጥ መሠረታዊ ሆኖ ሊጠቀስ የሚ ገባው አንድ ለውጥ በገባአ2 በአንቀጽ ስድሳ ሥር የተደነገገው ነው ። ይህ አን ቀጽ የኢ.ት.ብ.ባንክን የንብረት ስርጭት የሚመለከት ሲሆን በአገሪቱ የገንዘብ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በአገር ውስጥ ሕጋዊ የገንዘብ ኖቶች አወጣጥ ተግባርና በባንኩ የውጪ ሀብቱ መካከል የነበረውን መተሳሰር በመስበሩ ታሪ ካዊ ነው ። የዚህን ድንጋጌ ጉልህነት ለመገንዘብ ከ1976 ዓ.ም. በፊት የአገሪቱ የገንዘብ ኖቶች ሲወጡ የነበሩባቸውን ሁኔታዎችና እነዚህም በኢኮኖሚው ላይ የነበራቸውን ተጽዕኖ መለስ ብሎ መቃኘት አስፈላጊ ይሆናል ።

ምንም እንኳ የገንዘብ ኖቶችና ሳንቲሞችን ለማውጣት በ1945 ዓ.ም. መንግሥት ለኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ብቸኛ ሥልጣን የሰጠው ቢሆንም[46] በዚያውም ደግሞ ታትመው ከሚወጡት ኖቶች (ሳንቲሞችን አይጨምርም) ቢያንስ ቢያንስ ከመቶ ሰባ አምስት (75%) ያህል የሚገመት በወርቅ ፣ በብር ፤ (ሲልቨር) በውጭ አገር ገንዘብ ፣ በውጭ አገር ባንክ ሂሳብ ወይም ወዲያውኑ በውጭ አገር ገንዘብ ወይም በውጭ አገር ባንክ ሂሳብ ሊለወጡ በሚችሉ የዋስትና ገንዘቦች መልክ በዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ሂሳብ ፣ እንዲሁም ደግሞ ቀሪው ከመቶ ሃያ አምስት (25%) ግምት ያህል በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት የግምጃ ቤት ግዴታ ሰነዶች መደገፍ ይኖርበታል[47] ። በዚሁ ጊዜ በአገሩቱ ነፃ የምንዛሬ ሥርዓት ይካሄድ ነበር[48]። በዚህ ዓይነቱ አሠራር መሠረት ታትሞ የሚወጣውን የገንዘብ ኖት ልክና ብሎም በኢኮኖሚው ውስጥ የሚዘዋወር ገንዘብ ልክ የሚወሰነው በአገሪቱ ኢኮኖሚ ፍላጐት ሳይሆን ከውጪ ጋር በሚደረገው የንግድ ሚዛን (በትክክለኛው አነጋገር በክፍያ ሚዛን) ይሆናል። የንጉሠ ነገሥቱን የመንግሥት ግምጃ ቤት ግዴታ ለጊዜው ተወት አድርገን በውጭ አገር ቡናውን በአንድ ሺህ ብር የሸጠ አንድ የቡና ላኪ እናስተውል ፣ የኢት. መንግሥት ባንክ ይህን አንድ ሺህ ብር ሊከፍል የሚችለው የዚህኑ ያህል የውጭ አገር ምንዛሬ በጁ ሲያስገባ ነው ። ይኸው ላኪ(ወይም ሌላ ነጋዴ) በውጭ አገር ምንዛሬ ዋጋው አንድ ሺህ ብር የሚሆን ሸቀጥ ወደ አገር ያስገባ እንደሆነ ይህንኑ ያህል ገንዘብ ለኢት መ. ባንክ ማስረከብ አለበት ። እንደገና ለአገላለጽ እንዲቀል ከዚሁ ከመቶ ሃያ አምስት (25%) ግምጃ ቤት ግዴታ ድጋፍ ከሚለው ብንነሳ በመንግሥት ባንክ የሚወጣው የገንዘብ ኖት ልክና ብሎም በኢኮኖሚው ውስጥ በዝውውር ያለ ጠቅላላ የገንዘብ መጠን ይኸውም ከባንኮች ውጪ ያለ ገንዘብ ፣ የተጣራ ተንቀሳቃሽ ማጠራቀሚያ ሂሳብ ጠቅላላ ድምር ወደ ውጪ የሚወጡት ዕቃዎች ሸቀጦች ዋጋ ወደ አገር ውስጥ ከሚገቡት (ዕቃዎች) ሸቀጦች ዋጋ የሚያሳየውን ብልጫ ያህል ይሆናል ። የገቢና የወጪ የንግድ ዕቃዎች ዋጋ ተስተካክሎ ሲገኝ ለውጪ ዕቃዎች ንግድ የሚወጣው የገቢ የንግድ ዕቃዎችን ሥራ ለማካሄድ ባንኩ በሚያወጣው ኖት የሚጣጣ ስለሆነ ተጨማሪ ኖቶች አይወጡም ።

ይህም ማለት የአገር ውስጥ የገንዘብ አወጣጥ በመሠረቱ የሚፈጸመው የአገር ውስጥን ፍላጐት ሳይመለከት በባንኩ የተያዘው የኢንተርናሲዮናል መጠባበቂያ ሂሳብ መሠረት ነው ። የአገር ውስጥ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንደፈለገው ቢሆን ባንኩ ለማንኛውም ዓይነት ተግባር ቢያንስ በመቶ ሰባ አምስት (75%) ያህል በሆነ የውጭ ሀብት ያልተደገፈ የገንዘብ ኖቶች ሊያወጣ አይችልም ።

ይህ አሠራር የአገሪቱን የገንዘብ ቦርሳ በውጭ ኃይሎች ቁጥጥር ሥር በማድረጉ ብቻ አገሪቱ ነፃ ኢኮኖሚን ለመገንባት የሚያስፈልጋትን ጉልበት የመስለብና የማዳከም ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖ ነበረው ። ስለዚህም የብሔራዊ ኢኮኖሚው እንቅስቃሴ አቅጣጫና ፍጥነት በአገሪቱ ውስጥ በሚዘጋጁ ፖሊሲዎች ሳይሆን በዓለም አቀፍ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች የሚገዛና የሚታዘዝ ነበር። በኢኮኖሚው ውስጥ የሚዘዋወረው ገንዘብ መጠን በክፍያ ሚዛን የሚወሰኑ እውነታና ፤ የወደፊቱ ወደ ውጭ የሚላኩና የማይላኩ ዕቃዎች ምርት ቀደም ብለው የተፈጸሙትና ወደፊትም የሚጠበቁት ተግባሮች ክንውን ስለሆነ ፣ የምርትና ለሥራ ዕድል እድገት እንዲሁም የአገሪቱ የገቢ ንግድ ዕቃዎች ፍላጐት የውጭው ዓለም ከአገሪቱ በሚፈልገው ውጤት ጥብቅ ቁጥጥር ስር ዋሉ ።

የንግድ ሚዛንን መዛነፍ ሁኔታ እንኳ ወደ ጐን ብንተው ይህን የመሰለው የኖቶች አወጣጥ ለአገሪቱ ኢኮኖሚ መረጋጋትም አደገኛ ነው ። የንግድ ሚዛን ወደ አገሪቱ አድልቶ ሲገኝ ወይም ጥሩ አዝማሚያ ሲኖረው የገንዘብ አወጣጥና ፍላጐትም ይጨምራል ። ይህም ፍላጐትን ለመምራት የሚያስፈልጉ የአሠራር መዋቅሮች በሌሉበት የገንዘብ ኃይል መድከምና የዋጋ መናርን ያስከትላል ። በአንጻሩ ደግሞ የንግዱ ሚዛን ለአገሪቱ ተስማሚ ባልሆነ ሁኔታ ላይ ሲሆን የአ ገር ውስጥ የገንዘብ አወጣጥንና ፍላጐትን እንዲሁም የዋጋ መውደቅን ብሎም የምርት ውጤት መቀነስን ያስከትላል ። በአጠቃላይ አመለካከት ይህ አሠራር የውጭ እንቅስቃሴ በቅድሚያነት ተወስዶ የአገሪቱን ኢኮኖሚ በተቀጥላነት ከርሱ ጋር እንዲገናዘብ የሚጠይቅ በመሆኑ ባጭሩ ሊሳካ የማይችል ሁኔታ ነው እንላለን ።

በቡና ዋጋ መውደቅና ከዚሁ ጋር በተያያዙ እላይ ጠባያቸው በተጠቀሰው ችግሮች ሳቢያ በ1949 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) መንግሥቱ የአገር ውስጥ የገንዘብ ኖቶች የሚወጡበትን መሠረት መለወጥና በዚያውም የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ መቆጣጠሪያ ሥርዓትን የማቋቋም አስፈላጊነት ሊገነዘብ ቻለ ። ከ1949 እስከ 1950 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) ባለው ጊዜ ሁለት ዋና ዋና ሕጐች ወጥተው ነበር ። አን ደኛው የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ ሥራን ለመቆጣጠር ያስቻለ ሲሆን[49] ሌላ ኛው ደግሞ በአገር ውስጥ የሚወጡ ኖቶች በትንሹ በመቶ ሰባ አምስት (75%) በሚ ገመት የውጪ ሀብት መደገፍ የነበረባቸውን ቢበዛ ወደ ከመቶ ሠላሳ (30%) ዝቅ እንዲልና ቀሪው ሂሳብ በን.ነ.መ. የግምጃ ቤት ግዴታዎች እንዲሚላ ያደ ረገው ነው[50]። ይህ በአገር ውስጥ ሕጋዊ ገንዘብና በውጪ ሀብት መካከል ላለው ግንኙነት የተሻሻለ ማብራሪያ የሆነው ሕግ አንደኛው የገንዘብና የባንክ አዋጅ (ገባአ 1) ወጥቶ ሚዛኑን ቢበዛ በመቶ ሃያ አምስት (25%) እንዲሆን እስካደረገው ድረስ 1963 እ.ኤ.አ. ዓ.ም. ድረስ ሲሠራ ቆይቷል[51]። ስለዚህም ከ1950 እስከ 1963 ዓ.ም. ድረስ የአገር ውስጥ ሕጋዊ የገንዘብ ኖቶች እትመትና የዚሁ ውጤት የሆነው የአገር ውስጥ የገንዘብ አወጣጥ በአገሪቱ የውጪ ሀብት የመወሰኑ ሁኔታ ቀስ በቀስ እየቀነሰ ለመምጣት ችሏል ።

በገባአ2 መሠረት ንንደቀድሞው ለኢት.ብ.ባ. የገንዘብ ኖቶችን የማውጣት ብቸኛ ሥልጣን ሲሰጠው በዚያው ደግሞ ካለው ሀብት በከፊል በዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ሂሳብ እንዲያኖር ይጠበቅበታል[25]። ይሁንና ትልቁ ነገር በሚወጡት ሕጋዊ የገንዘብ ኖቶች መጠንና በዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ሂሳብ ውስጥ በሚኖረው ንብረት መካከል ምንም ዓይነት ግንኙነት እንዲኖር አለመ ደረጉ ነው ። በአንፃሩም በአዋጁ መንፈስ በቀጥታም ባይሆን የምንረዳው የሚ ወጡት የኖቶች ብዛት በአገሪቱ ኢኮኖሚ ፍላጐት መሠረት መሆኑንና በዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ሂሳብ የሚኖረው ንብረት ግምት ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዋጋ ፣ እንዲሁም ለዕዳ መክፈያ የሚወጣውን መሸፈን መቻል አለበት ። በዚህም መሠረት ገባአ2 በአገር ውስጥ ሕጋዊ ገንዘብ እትመትና ብሎም በአገሪቱ የገንዘብ አወጣጥና በዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ሂሳብ መካከል የነበረውን መተሳሰር በማስቀረት ፣ ለአንድ አገር ነፃ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ምንም አማራጭ የሌለውን ከውጪ ተጽዕኖ ነፃ በሆነ ሁኔታ በብሔራዊ አመራር የሚ ካሄድ የኢኮኖሚ ፖሊሲን ለማጠናከር ለሃያ አምስት ዓመታት ያህል ሲካሄድ የቆየውን ሂደት ከፍጻሜ አድርሶታል ።

## ለ/ የገንዘብ አወጣጥና የክሬዲት ሥራ በኢ.ብ.ባ. ቁጥጥር ሥር መዋሉ

የአገር ውስጥ ሕጋዊ የገንዘብ ኖቶች እትመት (እና ስለዚህም የአገሪቱ የገንዘብ አወጣጥ) ከአገሪቱ ቁጥጥር ውጪ ከሆኑና ከብሔራዊ ጥቅም ጋር ሊጋጩ ከሚችሉ ዓለም አቀፍ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች መሪር ተጽዕኖ የማላቀቁ እርምጃ መልካም አዝማሚያ የሚታይበት ሲሆን (አዋጁ) ገባአ2 የኢ.ት.ብ.ባ.ን ኃላፊነት በበለጠ ሰፋ ብሎ የሚከተሉትን እንዲጨምር አድርጓል ፤ እነዚህም ፥ (1) የተመዛዘነና የተፋፋመ የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲሠፍን የመርዳት ፣ (2) ከፍተኛ ምርት ፤ ሥራና ገቢን የማራመድን የማጠናከር ፣ (3) በገንዘባዊ ተቋሞች አማካኝነት የገንዘብን መጠን ከፍላጐት ጋር በማጣጣም የኢትዮጵያን የምርት ኃይሎች ዕድገት ማበረታታትና ማራመድ ናቸው ። የገንዘብ አወጣጥ መሠረቱ በመጀመሪያ ደረጃ የሚወጡት ሕጋዊ የገንዘብ ኖቶች ቀጥሎም በሌሎች ዋና ዋና ተቋሞች ማለትም በመንግሥት ፣ በሌሎች ባንኮችና የገንዘብ ድርጅቶች እንዲሁም የባንክ ሥራ ባልሆነው የግል ክፍለ ኢኮኖሚ የገንዘብ አጠቃቀም ስለሆነ ከውጪ ኃይሎች ተጽዕኖ ነፃ በሆነ መንገድ በኢኮኖሚ ውስጥ የሚዘዋወረውን የገንዘብ ልክ ከፍላጐት ጋር በትክክል አጣጥሞ በተግባር የመተርጐሙ ጉዳይ የሚወሰነው ባንኩ በራሱ ላይ ባለው ቁጥጥርና ከነዚህም ሶስት ተቋሞች ጋር በሚፈጸሙ የሥራ ግንኙነት ዓይነት ይሆናል ። ከነዚህም ሁለት ዓይነት ችግሮችን በቀላሉ ለመወጣት ይቻላል ። አንደኛ ባንኩ በራሱ ላይ የሚኖረውን ቁጥጥር በሚመለከት ረገድ በዕድሜም የጠና በመሆኑ በሚፈጽማቸው ማናቸውም ተግባሮች በጥንቃቄ የተጠኑና የበሰሉ እርምጃዎችንም የመውሰድ ኃላፊነት በሚገባ ሊሸከም ችሏል በሚል ግምት ላይ የተመሠረተ ነው ። ሁለተኛ የባንክ ሥራን በማይጨምረውና ከባንኩ ቀጥታ ቁጥጥር ውጪ የሆነውን (እና እስከ መስከረም 1979 ዓ.ም. እንደ ኤ.አ.አ. (በመቶ ሰባ ስድስት (76 %) ያህል የሚሆነው ከባንኮች ውጪ የሆነ ገንዘብ የያዘ [53]) የግል ክፍለ ኢኮኖሚ በሚመለከት ፥ ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች የሚጠይቁትን ወይም የሚከፍሉትን (እንደሁኔታው) የወለድ ደረጃ በመወሰንና ደምበኞቻቸውም ካሁኑ በበለጠ ሁኔታ የገንዘብ ድርጅቶቹ በሚሰጡት አገልግሎት እንዲጠቀሙ በመገፋፋት በገንዘብ ሀብታቸው አመራር ባንኮችን እንዲጠቀሙ በማድረግ የቁጥጥር ኃይሉን ሊያጐለብት ይችላል ። በባንኮችና በሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች በኩል ገንዘብ ነክ ሥራዎችን መቆጣጠርና ባንኩ ከመንግሥት ጋር ያለው ግንኙነት ይበልጥ ውስብስብ በመሆናቸው ባጭሩ ለመግለጽ እንሞክራለን ።

### 1/ ባንኮች ፥ ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶችና የኢ.ት.ብ. ባንክ

ከውጪ ሁኔታዎች ጋር በቀጥታ ያልተሳሰረ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ማካሄድ ብርቱ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ነገር በመሆኑ በትጋትና በብልሃት መያዝ ይኖርበታል ። በኢኮኖሚው ውስጥ የሚዘዋወረው የገንዘብ ልክ ከሚፈለገው በላይ ወይም በታች ከሆነ የአገሪቱ የውስጥ ኢኮኖሚ ሚዛን ተቃውሶ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መዳከምን ወይም የገንዘብ ኃይል መዳከምና የዕቃዎች ዋጋ መናርን ወይም ሁለቱንም ሊያስከትል ይችላል ። ስለዚህም የጊዜው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ፍላጐትና የገንዘብ አወጣጡ ሁልጊዜ ተመዛዛኝነት እንዲኖራቸው ማድረጉ የማያቋርጥ የቅርብ ክትትል የሚያስፈልገው ወሳኝ ተግባር ይሆናል ።

በሁለቱም አዋጆች ማለትም በገባአ 1ና በገባአ2 መሠረት [54] ለኢ.ት.ብ.ባ. የገንዘብ አወጣጥን የመቆጣጠር ኃላፊነት ተሰጥቶታል ። በኢትዮጵያ ሁኔታ ገንዘብ

ማለት ከባንክ ውጪ ያለ ገንዘብንና የተጣራ የተንቀሳቃሽ ሂሳብ ነው ። እንደ ሁለቱም ሕጐች የመቆጣጠሪያ ዘዴዎቹ ተመሳሳይ ቢሆኑም ባንኮችንና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶችን የሚመለከት አንድ በጣም ጠቃሚ የሆነ ድንጋጌ በገባአ2 ውስጥ በመጨመሩ የኢ.ት.ብ.ባንክ ከገባአ1 ይበልጥ በዚህ አዋጅ ሥር ጠንከር ያለ ሥፍራ አለው ። የገንዘብ አወጣጥን ለመቆጣጠር የኢ.ት.ብ.ባ. ሊጠቀምባቸው ከሚችለው መንገዶች ውስጥ ዋንኞቹ ባጭሩ ፤ ሀ/በቀጥታ የግዥና የሽያጭ አሠራር ፤ ለ/ ቅናሽ በማድረግና ሐ/ በመጠባበቂያ ሂሳብ ግዴታ ናቸው ። የኢ.ት.ብ.ባ. በነዚህ መንገዶች (በነጠላ ወይም በማዋሀድ) እንዴት እንደሚጠቀም በምሳሌ ለመግለጽ ከላይ በተብራራው መልክ ያለው የገንዘብ ልክ ለኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ከሚፈለገው በላይ ነው እንበል ። በዚህን ጊዜ የፖሊሲው ዓላማ በኢኮኖሚው ውስጥ በዝውውር ያለውን ገንዘብ መጠን መቀነስ ይሆናል ማለት ነው ። ቀጥታ የግዥና የሽያጭ አሠራር ለመጠቀም የወሰኑ እንደሆነ የመንግሥት የዋስትና ሠነዶችን (የግዴታ ሠነዶችን ፤ የግምጃ ቤት ሠነዶችን ፤ የውል ሠነዶችን ፤ ወዘተ.) ለባንኮች ፤ ለሌሎች የገንዘብ ድርጅቶችና ለሌሎች ሰዎች ለመሸጥ [55] በሚያስችለው ሥልጣኑ ይጠቀማል[56]። የኢ.ት.ብ. ባንክ በግዴታ ሠነዶች ሽያጭ ጊዜ የመንግሥት ዕዳ የምስክር ወረቀቶችን በማውጣት ገንዘብ ይሰበስብበታል ። በኢ.ት.ብ.ባ. ውስጥ ያለ ገንዘብ እንደ ውጪ ገንዘብ ስለማይቆጠር ይህ እርምጃ በባንክ ወጪ ካለ ገንዘብና ከማጠራቀሚያ ፍላጐት ውስጥ ለጊዜው የወጣውን ያህል ውጪ ከሚሆነው ገንዘብ ወዲያው ለማጉደል ይችላል ። የኢኮኖሚው ፍላጐት በዝውውር ላይ ካለው ገንዘብ ከፍ ብሎ ሲያገኘው ባንኩ ከላይ የተጠቀሰውን ሂደት መቀልበስ ይኖርበታል ።

በሌላ በኩል ደግሞ የኢ.ት.ብ.ባ. የገንዘብ አወጣጥን ለመቆጣጠር የቅናሽ ፖሊሲን ሊከተል ይችላል ። [57] ይህ መንገድ ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ከባንኩ እንዲበደሩ በማበረታታት ወይም እንዳይበደሩ ተስፋ በማስቆረጥ ሊሠራበት ሲችል የሚያገኙትም ብድር የክሬዲት ሥራ የመፍጠር ችሎታቸውን ያሰፋል ፤ ይህም በበኩሉ የገንዘብ አወጣጥን ከፍ ለማድረግ የሚችል ነው ። የኢ.ት.ብ.ባ. በአንድ ወቅት በዝውውር ላይ ያለው ገንዘብ ከኢኮኖሚው ፍላጐት ጋር የሚመጣጠን ወይም ከፍላጐት በላይ ሆኖ ሲያገኘውና ፤ በዚያው ወቅት ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ደግሞ የደምበኞቻቸውን ፍላጐት ለማርካት ከባንኩ ለመበደር ቢፈልጉ ፤ ለነርሱ የሚያበድርበትን ወለድ ተስፋ ሊያስቆርጥ በሚችል ደረጃ ከፍ ያደርጋል ። የገንዘብ አወጣጥ መጨመር አለበት ብሎ በሚያምንበት ጊዜ ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ግን የጥሬ ገንዘብ እጥረት ያለባቸው መሆኑን ሲገነዘብ የወለድ ደረጃውን ዝቅ በማድረግ ከርሱ እንዲበደሩ ይገፋፋቸዋል ።

የቀጥታ ግዥና ሽያጭ አሠራርና የቅናሽ ደረጃው አሠራር አስፈላጊ ቢሆኑም የገንዘብ አወጣጥ ከኢኮኖሚ ፍላጐት ጋር ብቻቸውን ፍሬያማ ሊያደርጉት አይችሉም ። ይህ የሚሆነው በባንክ ሥራ ኢንዱስትሪ ሁለት መሠረታዊ ጠባዮች ምክንያት ነው ። የመጀመሪያው እነዚህ ሁለት መንገዶች ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉት ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች የመንግሥት ዋስትና ሠነዶችን ለመግዛት (ወይም ለመሸጥ) ወይም ለመበደር ፈቃደኛ ፍላጐት ሲኖራቸው ብቻ በመሆኑ ነው ፤ አለበለዚያ ባንኩ ከፍላጐቱ ጋር እንዲስማሙ የሚያደርግበት ምንም መንገድ የለውም ፤ ሁለተኛ በኢ.ት.ብ.ባ. በባንኮችና በሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች መካከል የፍላጐት ልዩነት ወይም የጥቅም መጋጨት ሊኖር ይችላል ። የመጀመሪያው ፍላጐት የገንዘብ አቀራረብን ከፍላጐት ጋር ማስተካከል ሲሆን

የኋለኞቹ ግን ትርፍን ማካበት ነው ። በዚህ የተነሳም የኢ.ት.ብ.ባ. የዋስትና ሠነዶችን በመሸጥና ወይም የቅናሽ ደረጃን ከፍ በማድረግ የገንዘብ አወጣጥን መጠን ለመቀነስ ቢፈልግ ፣ ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ትርፍ በማካበት ዓላማቸው በመገፋፋት በደምበኞቻቸው የተጠራቀመውን የገንዘብ ሀብት እንደገና በማዘዋወር የገንዘብ አወጣጥ መጠን እንዲያሸቅብ ሊያደርጉ ይችላሉ ። የመጠባበቂያ ሂሳብ መኖር ግዴታና የገንዘብና ገንዘብ አከል ሀብቶች ሚዛን (የክሬዲት ሥራን የመጠንና የዓይነት ቁጥጥር አክሎ)[58] የኢ.ት.ብ.ባ. ፣ ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ሊያበድሩ የሚችሏቸውን ሂሳቦች የሚቆጣጠርባቸው መንገዶች ስለሆኑ በጣም አስፈላጊ ሆነው እናገኛቸዋለን[59]። የኢ.ት.ብ.ባ. የመጠባበቂያ ሂሳብ ግዴታን ለመጠቀም ይችላል[60]። ይህን መሣሪያ መጠቀም ማለት ባንኩ ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ከእዳቸው ውስጥ በመቶ የተወሰነውን ያህል በራሱ ሂሳብ እንዲያጠራቅሙ ሲያስገድድ ይህን ገንዘብ ለማበደርም ሆነ ለማንኛውም ነገር እንዳይጠቀሙ ያደርጋሉ ማለት ነው ። በዚሁ ዓይነት እንዲጠራቀም የተወሰነውን የገንዘብና የገንዘብ አከል ንብረቶች ሚዛን ለመሸፈን የተቀመጡት ሀብቶች ለሌላ ምንም ዓይነት ተግባር ሊውሉ አይችሉም[61]።

የቀጥታ ሽያጭ ግዥ የቅናሽ ደረጃ አሠራር ድንጋጌዎች ያለምንም ለውጥ ከገባአ 1 ወደ ገባአ2 በቀጥታ የተላለፈ ሲሆን[62] የመጠባበቂያ ሂሳብ ግዴታንና የገንዘብና ገንዘብ አከል ንብረቶች ሚዛንን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች የማይናቁ ማሻሻያዎች ተደርገውላቸዋል ። በገባአ1 ይኸው ሥልጣን ለኢ.ት.ብ.ባ. የተሰጠው ቢሆንም የመጠባበቂያ ሂሳብ ግዴታው ከፍተኛ ጣሪያ ከእዳው በመቶ ሀያ (20%) እንዲሆን ሲደነገግ ፣ ከአጭር ጊዜ ክፍያ እዳው የሚጠራቀመው የገንዘብና ገንዘብ አከል ንብረቶች ሚዛንም እንደዚሁ ከመቶ ሰላሳ (30%) እንዲሆን ወስኗል[63]። ይህም ማለት ገንዘብ በገፍ በዝውውር ላይ በሚሆንበት ጊዜ እንኳን ባንኮቹና ሌሎቹ የገንዘብ ድርጅቶቹ ከሚጠራቀመው እዳቸው ውስጥ በመቶ ሰማኒያውን(80%) ከአጭር ጊዜ ክፍያ እዳቸው ደግሞ ከመቶ ሰባ (70%) ያህሉን እንደልባቸው ለማበደር ስለሚችሉ በጊዜው የኢኮኖሚው ፍላጎት የሚጠይቀውን የገንዘብን ቅነሳ ፖሊሲ ሊያጨናግፉ ይችላሉ ። ይህንን ችግር በመገንዘብ ይመስላል የገባአ2 አዘጋጆች ከተጠራቃሚና ከአጭር ጊዜ ክፍያ እዳው መያዝ ያለበት የመጠባበቂያ ሂሳብ መጠን የመወሰን ሥልጣን ለባንኩ በመተው ባንኮቹና ሌሎቹ የገንዘብ ድርጅቶች ሊያበድሩ በሚችሉት ሂሳብ ላይ የመቶ በመቶ (100%) የቁጥጥር ችሎታ እንዲኖረው ያደረጉት[64]። ይህም ባንኩን ከቀድሞ በተሻለ ሁኔታ ላይ ያደርገዋል ። በነዚህ ድንጋጌዎች አማካኝነት የኢ.ት.ብ.ብ. ተፈላጊውን ውጤት እንደሚያስገኝ አድርጎ የመጠባበቂያና የጥሬ ገንዘብ ሚዛኑን በፈለገው አቅጣጫ ሊለዋ ውጠው ይችላል ።

## 2/ የክሬዲት ሥራ ቁጥጥር

በገባአ1 ሥር የኢ.ት.ብ.ባ.[65] በሚያወጣቸው ደምቦች አማካኝነት ለባንኮችና የገንዘብ ድርጅቶች ክሬዲት የሚሰጡበትን ሁኔታ ማስታወቅ ፣ ሁሉም ፤ ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ለደምበኞቻቸው በሚሰጡት ልዩ ልዩ ዓይነት ብድሮች ላይ የሚያስከፍሉትን ወለድ ደረጃና እንዲሁም ፣ የብድሩን ሁኔታ ፤ ጊዜ ፣ ተግባርና ወሰን ሊቀይስ ይችላል ። እነዚህ በቀጥታ ወደ ገባአ2 የተላለፉ ሲሆን[67] የኢ.ት.ብ.ባ. በሕዝብ ባለቤትነት ሥር ያሉ ድርጅቶች በቁጥጥራቸው

ሥር የሌሎትን ሀብቶች ለኅብረተሰቡ ጠቃሚ በሆነ ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማ ረጋገጥ የሂሳብ መዝገባቸውን ለመቆጣጠር የሚያስችለውን[67] ሥልጣን ተግባ ራዊ የሚያደርግበት ድንጋጌ በገባአ2 ተጨምሯል ። ባንኩ በሕዝብ ባለመብ ትነት ሥር ያሉ ድርጅቶች ሀብቶቻቸውን ያለአግባብ የሚጠቀሙበት መሆ ኑን ሲያምን ባንኮቹና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ምንም ዓይነት ብድር እንዳ ይሰጣቸው ሊያዝ ይችላል[68] ስለዚህ የኢ.ት.ብ.ባ. ለአገሪቱ እድገት አስተዋ ጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ ሥራዎች አስፈላጊውን ብድር እንዲያገኙና ለኢ. ኮኖሚው ጠቅላላ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የብድሩን መጠን የመወሰን ብቻም ሳይሆን የአገሪቱ ሀብቶች በትክክል ጥቅም ላይ መዋላቸውንም ለማረጋ ገጥ ይችላል ።

## ሐ/ የመንግሥትና የኢ.ት.ብ.ባ. ግንኙነት

በመንግሥትና በኢ.ት.ብ.ባ. መካከል ያለው ግንኙነት በገባአ2 ሥር የበለጠ የተጠናከረ ነው ። በገባአ1 ሥር በኢ.ት.ብ.ባ.ና በመንግሥት መካከል ያለው ግንኙነት በባንክና በአንድ ደምበኛ መካከል የሚኖር ዓይነት ሲሆን በገባአ2 ሥር ፤ ሀ/ የገንዘብ መረጋጋትንና የክፍያ ሚዛንን ለመጠበቅ ለ/ ኪሲራውን ለመሸፈን ለመንግሥት የፊናንስ አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል በመንግሥቱ የፊናንስ ፕላን ዝግጅት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋል[69]

ሁለተኛም አዋጁ መንግሥት ከኢ.ት.ብ.ባ. በሰስቱም የቀጥታ ብድር ፥ የግ ምጃ ቤት ሠነዶች ፡ የመንግሥት ዕዳ ሠነዶች መንገድ የሚያገኘው ብድር የሚ ታሰብበትን መደብ ቋሚ እንዲሆን አድርጐታል ። ካሁን ወዲያ መደቡ በአለፈው የበጀት ዓመት የተሰበሰበው መደበኛ ገቢ ይሆናል ። በተጨማሪም መደበኛውን ገቢ ከብድሩ መጠን ጋር ያለውን ሚዛን ከፍ በማድረግ የቀጥታ ብድሩ ሩብ ፥ የግምጃ ቤት ሠነዶች ሲሰና የመንግሥት እቃ ሠነዶች ግማሽ ያህል እንዲሆን አድርጓል ። የመደቡ ለውጥ ፤ የሚዛኖቹ ከፍ ማለትና የወለዱ ጣሪያ በመቶ ሶስት (3%) እንዲሆን መወሰን ሁሉ መንግሥት ለሚያከናውናቸው ተግባሮች ለሚያ ስፈልጉት የፊናንስ አገልግሎቶች በቂ ገንዘብ እንዲያገኝ ለማስቻል ነው[70]።

ከኢ.ት.ብ.ባ. ወደ መንግሥት የሚተላለፈው ገንዘብ መጠን ከፍ ማለትም መንግሥቱ በኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ውስጥ የሚጫወተውን ግንባር ቀደም ሚናና ፥ ኃላፊነቱም ቢያንስ ቢያንስ ካሁኑ ሁኔታ ለመገመት እስከምንችልበት ጊዜ ድረስ ከገቢው በጣም የላቀ ወጪ እንዲያደረግ የሚጠይቅ ከመሆኑ አንፃር ስናየው ተገቢ ይሆናል ።

## አዋጁና የኅብረተሰቡ ግብ አለመጣጣም

የኢትዮጵያ አብዮት ዓላማ ኅብረተሰባዊነትን መገንባት መሆኑ በማያሻማ ሁኔታ የተገለጸ ሲሆን ለዚህም ማናቸውም ገንዘብ ነክ ድርጅቶች በአመቺ ሁኔታ በታለመው ግብ አቅጣጫ አገልግሎታቸውን ማበርከት እንዳለባቸው እሌ የማ ይባል ሐቅ ነው ። ዳሩ ግን 1976ቱ አዋጅ ይህንን መሠረታዊ ዓላማ የሚቃረኑ አንዳንድ ሀሳቦች ያዘለ ሲሆን ዋና የሆኑት ሁለቱ ከዚህ በታች ተገልጸዋል ።

ሀ/ ነፃ ውድድር ስለመፍቀድ

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክና በሌሎች ባንኮች የገንዘብ ድርጅቶች በተ ለይም በንግድ ባንኮች ያለውን ግንኙነት በሚመለከት ከአንድ በላይ በመሆናቸው በማይቃረን ውድድር ተግባራቸውን ያከናውናሉ በሚል ግምት ላይ የተመሠረተ ነው ። ሆኖም ግን በሶሻሊስት አገሮችና በሌሎችም የኅብረተሰባዊነት መርሐ የሚከተሉ አገሮች የባንኮች ይዞታ ልምድ አንድ ማዕከላዊ የሆነ ባንክና በርሱ ቁጥጥር ሥር ዘመናዊ የአሠራር ስልትን የሚከተሉ ሌሎች ባንኮች መኖራቸውን ሲያስተምረን በመካከላቸው ምንም ዓይነት ውድድር አለመኖሩን ያስረዳል ። በኢትዮጵያ የባንኮች ዕድገት ሁኔታ ባለው አንድ የንግድ ባንክ አንፃር ከላይ የተጠቀሰውን ግምት የመከተሉ አዝማሚያ ተስፋ አነስተኛ ይሆናል ። ይህ አባባል በዚህ በኩል ያለውን ዕድገት ይቃወማል ማለት ሣይሆን ሕጉ በዝምታ ነፃ ውድድርን የመፍቀዱ ጉዳይ ከተያዘው ዓላማ ጋር የማይጣጣም አለመሆኑን ለማሳየት ነው ።

ለ/ ሁለተኛውና ከፍተኛ አለመጣጣም መኖሩን የሚያሳየው በብሔራዊ ባንኩና በመንግሥት መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመለከት ነው ። የሶሻሊስት ኢኮኖሚ በማዕከላዊ ፕላን ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ያለው አከራካሪ ጉዳይ የታቀደው ፕላን ተግባሩን በሥራ ላይ ለማዋል የገንዘብ ምንጮች ለዚህ ዓላማ ተገዥ መሆን አለባቸው ወይስ ፕላኑን በሥራ ላይ ለማዋል በቅድሚያ ወሳኙ የገንዘቡ መገኘት ጉዳይ ነው የሚለው ጭብጥ ነው ።

በኢትዮጵያ ሁኔታ የንግድ ባንኩ ሌሎች ባንኮችና የገንዘብ ድርጅቶች በማ ዕከላዊ ባንክ ቁጥጥር ሥር በመሆናቸው የተነሳ የመንግሥት የገንዘብ ምንጭ ከነዚሁ ብቻ በሚቀርብለት ላይ የተወሰነ ስለሆነ ከላይ ከተነሳው ጭብጥ ሁለተ ኛው አቀራረብ የሚያዋጣ አይመስልም ።

## መ ደ ም ደ ሚ ያ

ገባአ2 ምንም እንኳ ከአንቀጾቹ ብዙዎቹን ከቀደሙት ሕጎች የወረሰ ቢሆ ንም በአገሪቱ የገንዘብ ፖሊሲና በአመራሩ ከፍተኛ ለውጦች አድርጓል ።

የአገሪቱን የውስጥ የገንዘብ ፖሊሲ ለመጀመሪያ ጊዜ ከውጭ ኃይሎች ሽክምነት ወጥቶ ራሱን ችሎ እንዲቆም ፥ መንግሥት ሊጠቀምባቸው የሚችለ ውን የገንዘብ ሀብት መጠን ለመጨመርና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የአገሪቱን የገንዘብ ሥርዓት የመቆጣጠር ሥልጣን ከፍ ለማድረግ ችሏል ። ሆኖም ግን እነ ዚህ የታዩት መሻሻሎች የሚያኮሩ ቢሆኑም ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች በወለድ ደረጃዎችና በውስን በብድር አሰጣጡም በኩል በደምበኞቻቸው አካ ባቢ ብቻ የተወሰኑ ናቸው ። እነዚህ ሥልጣኖች ከጠቅላላው የገንዘብ አወጣጥ ጋር ሲመዛዘኑ ከባንክ ውጭ ያለው ገንዘብ ዝቅተኛ ሆኖ ለሚታይባቸው አገሮች በቂ ሲሆኑ ሶስት አራተኛው የሚወጣው ገንዘብ ከባንኮች ውጪ በሆነበት ኢት ዮጵያ ውስጥ ግን አጥጋቢ አይደሉም ። ይህንን ግዙፍ የተበተነ ሀብት ሰብሰብ አድርጎ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችሉ መንገዶችን የሚፈጥር ጠበቅ ያለ የገ ንዘብ ፖሊሲ አስፈላጊ ነው ። ይህ እስኪሆን ግን የኢት.(ብ)ባንክ የገንዘብ አወ ጣጥን የመቆጣጠር ችሎታ ያልተሟላ ሆኖ ይቆያል ።

## የ ግ ር ጌ ማ ስ ታ ወ ሻ

* ረዳት ፕሮፌሰርና የምርምር ተባባሪ ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

1. ስለባንክና ስለባንክ አገልግሎት ታሪክ ኢትዮጵያ ኦብዘርቨር ቅጽ 8 ቁ. 4 ይመልከቱ ።
2. የገንዘብና የባንክ አዋጅ 1963 ዓ. ም. (እ. ኤ. አ) ነ.ዋጅ ቁ. 206 ና የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ አዋጅ 1963 ዓ.ም. (እ. ኤ. አ.) አዋጅ ቁ. 211
3. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ቻርተር 1963 ዓ.ም. (እ. ኤ. አ.) ትዕዛዝ ቁ. 30
4. ቻርተሩና አዋጅ ቁ. 206 በየጊዜው የተሻሻሉ ስለሆነ በዚሁ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀምነው ለመጨረሻ ጊዜ በተሻሻሉት መሠረት ነው ።
5. ቻርተር አንቀጽ 8
6. ገባአ1 አንቀጽ 2
7. ቻርተር አንቀጽ 3
8. አንቀጽ 6
9. በአንቀጽ 2(5) (ሀ) ና (ለ) ሥር የተብራራ
10. አንቀጽ 9 (8)
11. አንቀጽ 9(7)
12. አንቀጽ 9(6)
13. ምዕራፍ 3 ከአንቀጽ 9— 14
14. ቻርተር አንቀጽ 9 እና ገባአ2 አንቀጽ 10 በቅደም ተከተሉ
15. ገባአ2 አንቀጽ 12(1) እና የቻርተሩን አንቀጽ 11(1) ፡ ገበአ2 አንቀፅ 12(2) እና የቻርተሩን አንቀጽ 12(2) ፤ ገባአ2 አንቀጽ 12 (3) (ሀ) እና (ለ) እና የቻርተሩን አንቀፅ 11 (3) (ሀ) እና (ለ) ን በቅደም ተከተል ይመለከቷል
16 . የቻርተሩ ምዕራፍ አራት ከአንቀጽ 15—21
17. የገንዘብና የባንክ አዋጅ ማሻሻያ ድንጋጌ ቁ. 54/1969 (እ.ኤ.አ) (ከዚህ በታች ድንጋጌ ብለን የምንጠራው)
18. አንቀጽ 13(3) ፤ (4) ፤ 7
19. ድንጋጌ አንቀጽ 2(ሀ) ና ገባአ ፤ አንቀጽ 29 እና 26(3)(ሀ)
21. ድንጋጌ አንቀጽ 2 (6)
22. አንቀጽ 26(3) (ለ) (3)
23. ድንጋጌ አንቀጽ 2(ሐ)
20. አንቀጽ 26(3)(ሀ)
24. አንቀጽ 26(3)(ሐ)
25. በምዕራፍ አራት ክፍል ሶስት ውስጥ የሚገኙትን አንቀጾች ያገናዝቡ
26. ገባአ 2 አንቀጽ 20—35 እና ገባአ 1 አንቀጽ 15—20
27. ገባአ 1 አንቀጽ 18ና ገባአ 2 አንቀጽ 33
28. ገባአ 1 አንቀጽ 13(5) እና ገባአ 2 አንቀጽ 26(3) (ለ) (2)
29. ገባአ 1 አንቀጽ 38(1) እና ገባአ 2 አንቀጽ 50
30. ገባአ 1 አንቀጽ 21—23 እና ገባአ 2 አንቀጽ 36—38
31. አንቀጽ 9(3)
32. አንቀጽ 37
33. አንቀጽ 49
34. ገባአ 1 አንቀጽ 3(1)
35. አንቀጽ 51
36. አንቀጽ 3(3)
37. አንቀጽ 52
38. ገባአ 1 አንቀጽ 8(1) ና ገባአ 2 አንቀጽ 60(1)
39. ገባአ 1 አንቀጽ 8(2)
40. አንቀጽ 60(1) ና (2)
41. አንቀጽ 61—67
42. አንቀጽ 69—74
43. አንቀጽ 68
44. ምንም እንኳ የባንክ ደብተሮችን በግል በምስጢር መያዝ ስለመቻሉ በ1943ቱ (እ. ኤ. አ.) የኢትዮጵያ ባንክ ቻርተር የተደነገገ ቢሆንም በገባአ 1 ግን ይህ አንቀጽ አልተጨመረም ነበር ።
45. የገባአ 2 ን (ችግሮች) እንከኖችና የገንዘብ ፖሊሲውን ውጤታማነት በሚመለከት በሌላ ሥራ ውስጥ የታተተበት ጉዳይ ስለሆነ እዚህ አንመለስበትም ፤ ለዚህም ከበፊታዱ ደግፌ ሞኔታሪ ፖሊሲ ፎር ዘ ሞብላይዘሽን ኤንድ ኢፌክቲቭ ዩቲሊዜሽን ኦፍ ፋይናንሻል ሪሶርስስ ገጽ 80—158 ያለውን ይመልከቱ

46. በ1945(እ. ኤ. አ) የወጣ የገንዘቦችና የሕግ ገንዘቦች አዋጅ አንቀጽ 3 (አዋጅ ቁ. 76)
47. አንቀጽ 4
48. እስከ 1949 ዓ. ም. (እ. ኤ. አ.) የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ ቁጥጥር አልነበረም ። የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ ማሻሻያ አዋጅ (የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁ. 127) ፤ 1949 (እ.ኤ.አ.) የወጣውን ይመልከቱ
49. የ1949(እ. ኢ.አ.) የገንዘብ ምንዛሬ አዋጅ ማሻሻያ) የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 127/1949
50. የ1950(እ.ኤ.አ) የገንዘቦችና የሕግ ገንዘቦች አዋጅ ማሻሻያ (አዋጅ 112/1950)
51. የገባእ 1 አንቀጽ 8(1)
52. አንቀጽ ሰባትና ስድሳን በተከታታይ ይመለከቷል ።
53. የኢት. ብ. ባ. በየሶስት ወሩ የሚወጣ መጽሔት (ኳርተር ሊቡለቲን) ቅጽ 6 ቁጥር 1 ፤ መጋቢት 1960 ።
54. አንቀጽ 2(9) እና 9(1) በተከታታይ
55. አንቀጽ 26(1) (ለ) ና አንቀጽ 26(3) (ሐ)
56. አንቀጽ 26(3(ለ) (4) ከላይ ከተጻፈው ሌላ
57. አንቀጽ 31
58. አንቀጽ 50 እና አንቀጽ 9(2) እንዲሁም የገባእ 2 አንቀጽ 34 በተከታታይ
59. የመጠባበቂያ ኃብት ግዴታና የገንዘብና ገንዘብ አከል ንብረቶች ሚዛን ሌላ መለስተኛ ዓላማቸው ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ኪሳራ ሲደርስባቸው ለደንበኞች የተጠራቀመ ሂሳብ ዋስትና በከፊል እንዲረጋገጥ ማድረግ ነው ።
60. አንቀጽ 33
61. ባሁኑ ጊዜ ለመጠባበቂያ የሚያስፈልገው ገንዘብ በተጠየቀ ጊዜ ለሚከፈሉ ሂሳቦች በመቶ አሥር (10)%፤ ለቁጠባ ሂሳቦችና ለተወሰነ ጊዜ ለሚቀመጡ ሂሳቦች በመቶ አምስት (5%) ነው ።
62. አንቀጽ 13(2) (ለ) ፣ 13(4) ፣ 13(5) 13(6) እና የገባእ 1 ን አንቀፅ 16 ከላይ ከተጠቀሱት የገባእ 2 አንቀፆች ጋራ ያስተያዩ
63. የገባእ 1 አንቀጽ 18(1) እና አንቀፅ 38 (1) በተከታታይ
64. አንቀጽ 33 ና 50
65. አንቀጽ 15—23
66. አንቀጽ 30—35
67. አንቀጽ 9(8)
68. አንቀጽ 9(7)
69. አንቀጽ 9(15) እና 26(2)
70. ከታህሣሥ ወር 1979 (እ. ኤ. አ.) የመንግሥት የአገር ውስጥ ዕቃ ብድር በጠቅላላው 1.2 ቢሊዮን ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ 26%ቀጥታ ብድር ፣ 24% የግምጃ ቤት ሰነዶች (የተስፋ ሰነዶችን ጨምሮ) እና ቀሪው 50%በመንግሥት ዕዳ ሰነዶች መልክ ነው ። ለዚህም በየሶስት ወሩ ታትሞ የሚወጣውን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ (ኳርተርሊ ቡለቲን) ቅጽ 6 ቁ. 1 መጋቢት 1980 ( እ.ኤ.አ)ይመለ ከቷል